DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የSY21-22፣ የ'Benjamin Banneker' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት: የመግቢያ (Admission) ሂደት የደረጃ መጠን (Rubric)

ከ9-12 ለሆኑ የክፍል ደረጃዎች

**ስለቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School) የመግቢያ (Admissions) መስፈርት:** በቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School) ውስጥ፣ ለትምህርት ከፍተኛ ስሜት ያላቸውን፣ ለማህበረሰቡ ቁርጠኝነት የሚያሳዩ፣ እና ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ አልፈው የሚሰሩ፤ ስኬትን ፈላጊዎችን ማግኘት እንፈልጋለን። አብዛኛዎቹ ስኬታማ አመልካቾች፣ ጽናታቸውን በGPA የስኬት ውጤታቸው ላይ ለማስመስከር የቻሉ፤ እንደሆኑ አውቀናል።

**ስለቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School) የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School) ውስጥ፣ በመጀመሪያ የሁሉንም አመልካቾች ሪፖርት ካርዶች፣ ጽሁፎች (essays)፣ እና ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) የምንመለከት ይሆናል። በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) የGPA የውጤት ደረጃ (Score) የለም። በመግቢያ (admissions) ሂደቱ ቀጣይ እርምጃው፣ ምንም አንድ አካል ባልሆነ የአመልካቹን ብቁነት ብቸኛ መወሰኛን ሳይጠቀም፣ እነዚህ እያንዳንዱ አካሎቶቹ፣ በእያንዳንዱ የውጤት ደረጃዎች ይሰጣቸዋል። ከፍተኛ የውጤት ደረጃን ያስመዘገቡ አመልካቾች፣ በቃለ-መጠይቁ እንዲካፈሉ ይጋበዛሉ።

የተጋበዙ አመልካቾች፣ ብቁነታቸው እንዲታይላቸው ለማድረግ፣ የቃለ-መጠይቁን አካል ማጠናቀቅ አለባቸው። በቃለ-መጠይቁ፣ የሚፈለገውን አነስተኛ (minimum) የውጤት ደረጃ የሆነውን፤ ከ15 ነጥቦች ውስጥ 12 ያገኙ ሁሉም ተማሪዎች፣ ለመግባት (admissions) ብቁ ተደርገው ይወሰዳሉ። በቃለ-መጠይቁ፣ ከ12 በታች ውጤት ያመጡ ተማሪዎች፣ ቃለ-መጠይቁን ጨምሮ አጠቃላይ የተጠራቀመ ውጤቶችን በአመልካቹ የመማር አካላቶች ውስጥ ባሉት ላይ ሁሉ መሠረት በማድረግ፤ 'ባነከር (Banneker) ያሰላዋል። ከፍተኛ የሆነ የተጠራቀመ የማመልከቻ የውጤት ደረጃዎች ያሏቸው ተማሪዎች፣ በየዓመቱ ቢያንስ 300 ብቁ የሆኑ አመልካቾችን ለመለየት ሲባል፤ ብቁ ሊሆኑም ይችሉ ይሆናል። ሁሉም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች እኩል የሆነ የደረጃ አሰጣጥን ያገኛሉ።

| የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች | መለኪያ (Weight) | ማስታወሻዎች: |
|---|---|---|
| የቀለም ትምህርት የመስፈርት ምልከታ (GPA) | 30% (15/50 ነጥቦች) የሆነ፣ ማለፍ የሚገባው መስፈርት (Threshold criteria) | የቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School)፣ እንደ የሪፖርት ካርድ ምልከታ በማድረግ፣ የውጤት ደረጃዎችን (GPA)ን ይመለከታል። በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) GPA ወይም አስፈላጊ የሆነ የፈተና የውጤት ደረጃ የለም፤ ነገር ግን ማመልከቻው፣ ለመግባት (admission) እንዲታይ ለማድረግ፣ የሪፖርት ካርድ መግባት አለበት።<br><br>በተለምዶ፣ በፕሮግራማችን ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች፣ በሁለቱም ምልከታ በተደረገባቸው የሪፖርት ካርዶች ላይ የ2.5 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ GPA አላቸው። ሆኖም፣ አነስተኛ GPAዎች ያሏቸው ተማሪዎች፣ ትክክለኛ የሆነ እርዳታን እና ስልቶችን ሲያገኙ ስኬትን ማግኘት እንደሚችሉ ለማወቅም ችለናል። በSY19-20 የPARCC መሰረዝ ምክንያት፤ DCPS የPARCC ወይም የሌላ ደረጃውን የጠበቀ የፈተና ውጤት እንደ የSY21-22 የመግቢያ (admissions) ፈተናዎች አድርገው አያስገቧቸውም። |
| ጽሁፍ (Essay): በMSDC ማመልከቻ ውስጥ | 10% (5/50 ነጥቦች) የሆነ፤ ማለፍ የሚገባው መስፈርት (Threshold criteria) | ልክ እንደ ቃለ-መጠይቁ፣ በMSDC ማመልከቻ ውስጥ ያለው ጽሁፍ (essay)፤ በፕሮግራማችን ውስጥ ያለውን የተማሪውን ፍላጎት፣ ለማህበረሰቡ ቁርጠኝነት የሚያሳዩ፣ እና የግል ጽናታቸውን የማንጸባረቅ ልምዶች ያሏቸውን ለማግኘት ይጠቀምበታል።<br><br>ጽሁፎች (Essays) የውጤት ደረጃ የሚሰጣቸው፣ እና ይህ የውጤት ደረጃ ከተማሪው አጠቃላይ ብቁነት የውጤት ደረጃ ላይ በ10% አካውንት ይደረጋል። ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ወቅት በሙሉ አዘውትረው መፃፍ ይጠበቅባቸዋል፤ ስለሆነም፣ ለጽሁፍ (essay) የውጤት አሰጣጥ ላይ፣ ሰዋሰውና ቃላትን (grammar and vocabulary) ጨምሮ፣ በአፃፃፍ ቴክኒኮች ላይ ያተኩረ ይሆናል። |
| ድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | 60% (30/50 ነጥቦች) የሆነ፣ | የቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School)፣ የተማሪውን የትምህርት ቤት ውስጥ ተሞክሮ የበለጠ ለመረዳት |

| | | |
|---|---|---|
| | ማለፍ የሚገባው መስፈርት (Threshold criteria) | እና የቀለም ትምህርት ባገኙት የውጤት ይዘት ላይ ለመስጠት በማለት፤ የአስተማሪን ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠቀማል። አብዛኛዎቹን የባነከር (Banneker) አመልካች የምልከታ መስፈርትን ያካተተ የድጋፍ መስጫዎች (Recommendations)፣ እና እንደ ወሳኝ የሆነ አካል ተደርገው ስለተማሪው ለማወቅ እና ያላቸውን ተሞክሮዎች ለመመልከት ይጠቅማሉ።<br><br>የቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School)፣ እያንዳንዳቸው 10 ነጥቦችን በከፍተኛነት (maximum) ያላቸውን፣ ሦስት የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይፈልጋል። በየግል የገቡ የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) በራሳቸው በኩል እንዲከታተሉ እና የድጋፍ ሰጪውን የኢሜል አድራሻዎች ትክክለኛነት በማረጋገጥ የተማሪውን በእጅጉ የተሟላ ምስል በተቻለ መጠን ለማስገኘት፤ ተማሪዎች እና ቤተሰቦችን ክትትል እንዲያደርጉ አጥብቀን እናበረታታል። ሆኖም፣ ተማሪዎች ላልተሟሉ ወይም ለጠፉ የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ቅጣት አይደርስባቸውም፤ እና ወደ ቃለ-መጠይቅ ደረጃው በተገኘው የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ላይ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ እንዲገመገም ይደረጋል። |
| **ለማለፍ የሚገባው መስፈርት (Threshold criteria) ላይ፣ ከፍተኛ ውጤት ያላቸው አመልካቾች፣ ለመግቢያው (admissions) ሂደት ወደሆነው ወደ የቃለ-መጠይቁ አካሉ እንዲቀጥሉ ይደረጋል።** | | |
| ቃለ-መጠይቅ | 15 ነጥቦች የሚቻል ይሆናል | የቤንጃሚን ባነከር አካዳሚክ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Benjamin Banneker Academic High School)፣ የጋለ ስሜት ያላቸውን እና ለማህበረሰቡ ትጋትን የሚያሳዩ እንዲሁም በመላው ዓለም የተወዳዳሪነት ጽናትን የሚያሳዩ ተማሪዎችን ለይቶ በማውጣት ላይ ከፍተኛ እምነት አለው።<br><br>ወደ ቃለ-መጠይቁ ከተጋበዙ፣ እጩዎቹ ከወላጅ/አሳዳጊ ወይም ከሌላ የቅርብ የቤተሰብ አባል (ከ18 ዓመት በላይ የሆነ) ወይም ሌላ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው ጋር (እንደ አሰልጣኝ፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት መሪ/mentor)፤ ተማሪዎችን በመደበኛነት ከሚረዷቸው ጋር አብሮ መምጣት አለባቸው። እጩዎች በጣም የቅርብ ጊዜ የሆነ የተማሪ ሪፖርት ካርድን በቃለ-መጠይቁ ለመወያየት ማምጣትን ማቀድ ይገባቸዋል።<br><br>በጤና ሁኔታዎች እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY21-22 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ ሊከናወን ይችላል።<br><br>በቃለ-መጠይቁ፣ አስፈላጊ የሆነውን በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) የውጤት ደረጃን፤ 12 ወይም ከዚያ በላይ ያገኙ ሁሉም ተማሪዎች፣ ለመግባት (admissions) ብቁ ተደርገው ይወሰዳሉ። በቃለ-መጠይቁ፣ ከ12 በታች ውጤት ያመጡ ተማሪዎች፣ ቃለ-መጠይቁን ጨምሮ አጠቃላይ የተጠራቀመ ውጤቶችን በአመልካቹ የመማር አካላቶች ውስጥ ባሉት ላይ ሁሉ መሠረት በማድረ፤ ‘ባነከር (Banneker) ያሰላል። ከፍተኛ የሆነ የተጠራቀመ የማመልከቻ የውጤት ደረጃዎች ያሏቸው ተማሪዎች፣ በየዓመቱ ቢያንስ 300 ብቁ የሆኑ አመልካቾችን ለመለየት ሲባል፤ ብቁ ሊሆኑም ይችሉ ይሆናል። ሁሉም ብቁ የሆኑ ተማሪዎች እኩል የሆነ የደረጃ አሰጣጥን ያገኛሉ። |

## SY21-22 ባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC): የመግቢያ (Admission) ሂደት የደረጃ መጠን (Rubric)

*ለክፍል ደረጃዎች: 9 እና 10*

**ስለ ባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC)፣ የመግቢያ (Admissions) መስፈርት:** በባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC) ውስጥ፣ ተነሳሽነትን የሚያሳዩ፣ ምሁራዊ የመሆን ፍላጎት፣ እና በቀለም ትምህርት ላይ የሚገጥሙ ፈታኝ በሆኑ ነገሮች የሚነሳሱ፣ እና በሌጋ ዕድሜያቸው ወደ ኮሌጅ የኮርስ ስራዎች ዘለው የሚገቡ ጉጉት ያደረባቸውን፣ ምሁሮችን እንፈልጋለን።

**ስለ ባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ ( Bard High School Early College DC)፣ የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ (Bard High School Early College) ውስጥ፣ የመግቢያ (admissions) ሂደታችን የሚያካትተው፣ ጽሁፍ (essay)፣ ቃለ-መጠይቅ (በዙም/zoom አማካኝነት)፣ እና ሁለት የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations)ን በMy School DC ማመልከቻ አማካኝነት ማስገባት ነው። ለእያንዳንዱ እጩ፣ እያንዳንዱን የመግቢያ (Admissions) ክፍሎችን ከግምት ውስጥ የምናስገባ እና ሁሉም አመልከቾች አንድ ዓይነት በሆነ የደረጃ መጠን (rubric) ይመዘናሉ። ምንም አንድ የመግቢያ (Admissions) ክፍል ብቻውን ለብቁነት መወሰኛ ሆኖ አይወሰድም። ሁሉም ተማሪዎች፣ ለመግባት (admissions) ብቁነታቸው እንዲታይላቸው ለማድረግ፣ የቃለ-መጠይቅን እና ጽሁፍ (essay)ን ማጠናቀቅ አለባቸው።

እያንዳንዱ ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሰረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚመዘን ይሆናል። አመልካቾች፣ ለመግባት (admissions) ብቁ ሆነው ለመገኘት፣ በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) ጠቅላላ የውጤት ደረጃ የሆነውን ከ14 ነጥቦች ውስጥ 10፣ ማግኘት አለባቸው። 10 ነጥቦችን እና ከዚያ በላይ ያገኙ ሁሉም ተማሪዎች፣ ለመግባት (admissions) ብቁ የሚሆኑ እና በነጥቦቻቸው የውጤት ደረጃ ቅደም ተከተል መሠረት ደረጃ ይሰጣቸዋል።

| **የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች** | **መለኪያ (Weight)** | **ማስታወሻዎች:** |
|---|---|---|
| ቃለ-መጠይቅ | ~ 36%( 5/ 14 ነጥቦች) | **የባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC)፣** በማህበረሰባቸው ውስጥ የለውጥ ወኪል ለመሆን የጋለ ስሜት ያላቸው እና ለመማር ፍቅር ያላቸውን ተማሪዎችን ለመለየት ጥልቅ የሆነ እምነት አለው። ራሱን የሚገልጽ እና አዲስ ነገሮችን ለመማር ደስተኝነትን የሚያንፀባርቅ ተማሪን ማግኘት እንፈልጋለን።<br><br>በጤና ሁኔታዎች እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY21-22 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ ይከናወናል።<br><br>ቃለ-መጠይቁ የውጤት ደረጃ የሚሰጣቸው፣ እና ይህ የውጤት ደረጃ ከተማሪው አጠቃላይ ብቁነት የውጤት ደረጃ ላይ በ36% አካውንት ይደረጋል። |
| ጽሁፍ (Essay): | ~36% (5/14 ነጥቦች) | ልክ እንደ ቃለ-መጠይቁ፣ ጽሁፉም (essay) የተማሪውን በፕሮግራማችን ላይ ያለውን ፍላጎት፣ ለማህበረሰቡ ያለውን ቁርጠኝነት፣ እና ተማሪዎች አገናዝበው የማሰብ ችሎታዎቻቸው ላይ ያላቸውን እውቀት እንዴት እንደሚያሳዩ ለማወቅ ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ ጽሁፍ (essay) በMSDC ማመልከቻ ውስጥ የሚጠናቀቅ ይሆናል።<br><br>ጽሁፎች (Essays) የውጤት ደረጃ የሚሰጣቸው፣ እና ይህ የውጤት ደረጃ ከተማሪው አጠቃላይ ብቁነት የውጤት ደረጃ ላይ በ 36% አካውንት ይደረጋል። ምንም እንኳን ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ወቅት በሙሉ አዘውትረው መፃፍ ቢጠበቅባቸውም፣ ለጽሁፍ (essay) የደረጃ መጠኑ (rubric)፣ በቴክኒካል የአፃፃፍ ችሎታዎች ላይ፤ እንደ ሰዋሰውና ቃላት (grammar and vocabulary) ላይ ያተኮረ አይሆንም። |
| የድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | ~ 29% ( 4/ 14 ነጥቦች) | **የባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC) ፣** የተማሪውን የትምህርት ቤት ውስጥ ተሞክሮ የበለጠ ለመረዳት እና ጽሁፎቻቸውን (essay) እና ቃለ-መጠይቅ ይዘትን ለመስጠት በማለት፤ የአስተማሪ ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠቀማሉ።<br><br>የባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቅድመ ኮሌጅ (Bard High School Early College)፣ ሁለት የድጋፍ መስጫዎች (recommendations)ን ይፈልጋል። በተጠየቀው አስተማሪ አንድ ብቻ ተሞልቶ ከተጠናቀቀ፣ በገባው አንድ ድጋፍ መስጫ (recommendation) ላይ መሠረት በማድረግ ተማሪውን እንገመግማለን። ምንም ዓይነት ድጋፍ መስጫ (recommendations)ን ካላስገቡ፣ ትምህርት ቤቱ ወደ ~15% መጠን (weight) የሚጠጋ ( 2 ነጥቦች)ን ወደ ቃለ-መጠይቁ እና ጽሁፉ (essay) ይጨምራል። |

## SY21-22 ባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC): የመግቢያ (Admission) ሂደት የደረጃ መጠን (Rubric)

*ተዛማጅ የሆኑ የክፍል ደረጃዎች፡ 11ኛ*

**ስለ ባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC)፣ የመግቢያ (Admissions) መስፈርት፡** በባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC) ውስጥ፣ ተነሳሽነትን የሚያሳዩ፣ ምሁራዊ የመሆን ፍላጎት፣ እና በቀለም ትምህርት ላይ የሚገጥሙ ፈታኝ በሆኑ ነገሮች የሚነሳሱ፣ እና በለጋ ዕድሜያቸው ወደ ኮሌጅ የኮርስ ስራዎች ዘለው የሚገቡ ጉጉት ያደረባቸውን፤ ምሁሮችን እንፈልጋለን።

**ስለ ባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ ( Bard High School Early College DC)፣ የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC) ውስጥ፣ 11ኛ ክፍሎች ውስጥ ለሚያድጉ፣ የመግቢያ (admissions) ሂደታችን የሚያካትተው፣ ጽሁፍ (essay)፣ የርቀት በምናባዊ (virtual) ቃለ-መጠይቅ (በዙም/zoom አማካኝነት)፣ እና ሁለት የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations)ን እና የትምህርት ማስረጃ (transcript)ን፤ በMy School DC ማመልከቻ አማካኝነት ማስገባት ነው። ለእያንዳንዱ እጩ፣ እያንዳንዱን የመግቢያ (Admissions) ክፍሎችን ከግምት ውስጥ የምናስገባ እና ሁሉም አመልከቾች አንድ ዓይነት በሆነ የደረጃ መጠን (rubric) ይመዘናሉ። ምንም አንድ የመግቢያ (Admissions) ክፍል ብቻውን ለብቁነት መወሰኛ ሆኖ አይወሰድም። ሁሉም ተማሪዎች፣ ለመግባት (admissions) ብቁነታቸው እንዲታይላቸው ለማድረግ፣ የቃለ-መጠይቅን እና ጽሁፍ (essay)ን ማጠናቀቅ አለባቸው።

እያንዳንዱ ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሰረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚመዘን ይሆናል። አመልካቾች፤ ለመግባት (admissions) ብቁ ሆነው ለመገኘት፣ አነስተኛ መጠን (minimum) ጠቅላላ የውጤት ደረጃ የሆነውን ከ17 ነጥቦች ውስጥ 12፣ ማግኘት አለባቸው። 12 ነጥቦችን እና ከዚያ በላይ ያገኙ ሁሉም ተማሪዎች፣ ለመግባት (admissions) ብቁ የሚሆኑ እና በነጥቦቻቸው የውጤት ደረጃ ቅደም ተከተል መሰረት ደረጃ ይሰጣቸዋል።

| የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች | መለኪያ (Weight) | ማስታወሻዎች፡ |
|---|---|---|
| ሪፖርት ካርድ ምልከታ (GPAን ጨምሮ) | ~ 18% ( 3/ 17 ነጥቦች) | **ባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC)**፣ እንደ የሪፖርት ካርድ ምልከታ በማድረግ፣ የውጤት ደረጃዎችን (GPA)ን ይመለከታል። በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) GPA ደረጃ የለም፤ ነገር ግን ማመልከቻው፣ ለመግባት (admission) እንዲታይ ለማድረግ፣ የሪፖርት ካርድ መግባት አለበት።<br><br>በፕሮግራማችን ውስጥ የሚመጡ ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች፣ ብዙውን ጊዜ የ2.0 ነጥብ ወይም ከዚያ በላይ GPA ያላቸው መሆኑ ሆነነው አግኝተናቸዋል። ሆኖም፣ አነስተኛ GPAዎች ያሏቸው ተማሪዎች፣ ትክክለኛ የሆነ እርዳታን እና ስልቶችን ሲያገኙ ስኬትን ማግኘት እንደሚችሉ ለማወቅም ችለናል። |
| ቃለ-መጠይቅ | ~ 29% ( 5/ 17 ነጥቦች) | **የባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ ኮሌጅ ዲሲ** (**Bard High School Early College DC**)፣ በማህበረሰባቸው ውስጥ የለውጥ ወኪል ለመሆን የጋለ ስሜት ያላቸው እና ለመማር ፍቅር ያላቸውን ተማሪዎችን ለመለየት ጥልቅ የሆነ እምነት አለው። ራሱን የሚገልጽ እና አዲስ ነገሮችን ለመማር ደስተኝነትን የሚያንፀባርቅ ተማሪን ማግኘት እንፈልጋለን።<br><br>በጤና ሁኔታዎች እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY21-22 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ ይከናወናል።<br><br>ጽሁፎች (ቃለ-መጠይቅ) የውጤት ደረጃ የሚሰጣቸው፣ እና ይህ የውጤት ደረጃ ከተማሪው አጠቃላይ ብቁነት የውጤት ደረጃ ላይ በ29% አካውንት ይደረጋል። |

| | | |
|---|---|---|
| ጽሁፍ (Essay): | ~ 29% ( 5/ 17 ነጥቦች) | እንደ ቃለ-መጠይቁ በተመሳሳይነት፣ በMSDC ማመልከቻ ውስጥ ያለው ጽሁፍ (essay)፤ በፕሮግራማችን ውስጥ ያለውን የተማሪውን ፍላጎት፣ ለማህበረሰቡ ቁርጠኝነት የሚያሳዩ፣ እና አገናዝበው የማሰብ ችሎታዎቻቸው ላይ ያላቸውን እውቀት ለማሳየት ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ ጽሁፍ (essay) በMSDC ማመልከቻ ውስጥ የሚጠናቀቅ ይሆናል።<br><br>ጽሁፎች (Essays) የውጤት ደረጃ የሚሰጣቸው፣ እና ይህ የውጤት ደረጃ ከተማሪው አጠቃላይ ብቁነት የውጤት ደረጃ ላይ በ29% አካውንት ይደረጋል። ምንም እንኳን ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ወቅት በሙሉ አዘውትረው መፃፍ ቢጠበቅባቸውም፣ ለጽሁፍ (essay) የደረጃ መጠኑ (rubric)፣ በቴክኒካል የአፃፃፍ ችሎታዎች ላይ፤ እንደ ሰዋሰውና ቃላት (grammar and vocabulary) ላይ ያተኮረ አይሆንም። |
| የድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | ~ 24% ( 4/ 17 ነጥቦች) | **የባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቅድመ ኮሌጅ ዲሲ (Bard High School Early College DC)፣** የተማሪውን የትምህርት ቤት ተሞክሮ የበለጠ ለመረዳት እና ለሪፖርት ካርዳቸው ይዘትን ለመስጠት፤ የአስተማሪን ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠቀማል።<br><br>የባርድ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቅድመ ኮሌጅ (Bard High School Early College)፣ ሁለት የድጋፍ መስጫዎች (recommendations)ን ይፈልጋል። በተጠየቀው አስተማሪ አንድ ብቻ ተሞልቶ ከተጠናቀቀ፣ በገባው አንድ ድጋፍ መስጫ (recommendation) ላይ መሠረት በማድረግ ተማሪውን እንገመግማለን። ምንም ዓይነት ድጋፍ መስጫ (recommendations)ን ካላስገቡ፣ ትምህርት ቤቱ ወደ ~15% መጠን (weight) የሚጠጋ ( 2 ነጥቦች)ን ወደ ቃለ-መጠይቁ እና ጽሁፉ (essay) ይጨምራል። |

## SY21-22 የኮሎምብያ ሃይትስ የትምህርት ካምፓሶች (Columbia Heights Education Campus (CHEC)፣ የመግቢያ (Admissions) የደረጃ መጠን (Rubric)

*ለክፍል ደረጃዎች፡ ከ9- 12 (ሁሉም የክፍል ደረጃዎች)*

**ኮሎምብያ ሃይትስ የትምህርት ካምፓሶች (Columbia Heights Education Campus) የመግቢያ (Admissions) መስፈርት:** በኮሎምብያ ሃይትስ የትምህርት ካምፓሶች (Columbia Heights Education Campus (CHEC) ውስጥ፣ በርካታ ቋንቋዎች የሚያዳብሩ እና ምሁራዊ የመሆን ፍላጎት ያላቸውን፣ በሕይወታቸው ሙሉ ለመማር ትጋትን የሚያሳዩ፣ ለማህበረሰቡ ለማበርከት ጽኑ ስሜት ያላቸው፣ እና ማህበራዊ ፍትህን ለማስገኘት ጥያቄ ያላቸውን፣ ለማግኘት ይፈልጋል። ለእድገት አዕምሮዋቸውን አሳምነው የሚጓዙ፣ እና ልቆ ለመሄድ እና ለፈጠራ በማያቋርጥ ሁኔታ የሚገፋትን፤ በይበልጥ ስኬታማ የሆኑ አመልካቾችን እንፈልጋለን።

**ኮሎምብያ ሃይትስ የትምህርት ካምፓሶች (Columbia Heights Education Campus) የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በኮሎምብያ ሃይትስ የትምህርት ካምፓሶች (Columbia Heights Education Campus (CHEC) ውስጥ፣ የማስገቢያ ሂደታችን የሚያካትተው፤ የፍላጎት የዳሰሳ ጥናት፣ ሁሉት የአስተማሪ የድጋፍ መስጫዎች (recommendations)፣ እና የሪፖርት ካርድ ምልከታ፤ ሲሆኑ፣ እነዚህ ሁሉ በ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻ አማካኝነት መግባት አለባቸው። በተጨማሪም፣ የወደፊት ተማሪው፣ በቃለ-መጠይቁ መሳተፍ አለበት። ለእያንዳንዱ እጩ፣ እያንዳንዱን የመግቢያ (Admissions) ክፍሎችን ከግምት ውስጥ የምናስገባ እና ሁሉም አመልከቾች የውጤት ደረጃ ይሰጣቸዋል። ምንም አንድ የመግቢያ (Admissions) ክፍል ብቻውን ለብቁነት መወሰኛ ሆኖ አይወሰድም። ሁሉም ተማሪዎች፣ በጣም የቅርብ ጊዜ የሆነውን የተርሙን ሪፖርት ካርድ እና የቀድሞውን ዓመት የመጨረሻ ሪፖርት ካርድ ማስገባት አለባቸው። እንደ ጀማሪ ተማሪ (freshman) የማያመለክቱ ሁሉ፤ በምርቃት ጊዜ በሚደረገው ስብሰባ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት፣ የቅርብ ጊዜ የትምህርት ውጤት ማረጋገጫቸውን (transcript) እንዲያስገቡ በእጅጉ እናበረታታለን። ለ'CHEC' የምርቃት መስፈርቶች የሚያስፈልጉትን [እዚህ](#) መመልከት ይቻላል።

<u>በአሁኑ ወቅት የኮሎምብያ ሃይትስ የትምህርት ካምፓሶች (Columbia Heights Education Campus)፣ የ8ተኛ ክፍል ተማሪዎች</u>

የኮሎምብያ ሃይትስ የትምህርት ካምፓሶች (Columbia Heights Education Campus (CHEC)፤ ሁለቱንም፣ የአጎራባች፤ እንዲሁም በመብት (by-right) የመካከለኛ ትምህርት ቤትን ከ6-8 ክፍሎችን እና ተመራጭ (selective) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ከ9-12 ክፍሎችን ይሰጣል። በCHEC ውስጥ በ8ተኛ ክፍል ውስጥ ገብተው የሚማሩ፣ ለ9ኛ ክፍል ማመልከቻ ሂደቱን ያጠናቀቁ ሁሉም ተማሪዎች፣ በማመልከቻቸው ላይ ካለው ትምህርት ቤት የበለጠ ደረጃ ካለው ትምህርት ቤት ጋር እስካልተዛመዱ ጊዜ ድረስ ብቻ፣ በCHEC (9ኛ ክፍል) ለመግባት ዋስትና ያገኛሉ።

እያንዳንዱ የማመልከቻ ሂደት ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሠረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚለካ ይሆናል። አመልካቾች፣ ለመግባት ብቁ ሆነው እንዲወሰዱ፣ እና ባመጡት የነጥብ ደረጃ መሰረት ደረጃ እንዲሰጣቸው፤ ቢያስን፣ ቢያንስ፤ የአጠቃላይ የውጤት ደረጃው 70/100 የሆነን ማግኘት አለባቸው።

| የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች | መለኪያ (Weight) | ማስታወሻዎች: |
|---|---|---|
| ሪፖርት ካርዶች ምልከታ (GPAን እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት/attendance የሚያካትት) | 30% | CHEC፣ እንደ የሪፖርት ካርድ ምልከታ አንዱ አካል በማድረግ፤ የክፍል ደረጃ ውጤቶችን እና በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትና አለመገኘት (Attendance) ይመለከታል። በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) አማካኝ (average) ወይም በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትና አለመገኘት (Attendance) መለኪያ የሚያስፈልግ አይሆንም፤ ነገር ግን ማመልከቻው ተጠናቋል ብሎ ለማስገባትና መግባትን (admission) ከግምት ውስጥ ለማስገባት፣ የሪፖርት ካርድ መግባት አለበት።<br><br>በተለምዶ፣ በCHEC ውስጥ ስኬትን ለማግኘት ዝግጁ የሆኑ ተማሪዎች፣ የ2.5 GPA ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ውጤት እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት ደረጃቸው 90% ወይም ከዚያ በላይ ነው። ልዩ የሆነ ጉዳዮችን የመመልከት አስተያየት የሚወሰድ እና ቤተሰቦች ረዳት ርዕሰ-መምህር ጋልቫን (Galván) በ Edilberto.Galvan@k12.dc.gov አግኝተው፣ ስለዚህ ሂደት የበለጠ ለማወው ማነጋገር ይችላሉ። |
| ቃለ-መጠይቅ | 25% | CHEC፤ ለቀለም ትምህርቶች የጋለ ስሜት ያላቸውን፣ ለቋንቋዎች፣ እና ለፍትህ፣ ለማህበረሰቡ ቁርጠኝነት የሚያሳዩ፣ እና አልበገር ባይነት እና ጽናትን የሚያንጸባርቁ፤ እነዚህን ሁሉ ማህበራዊ ፍትህን ለማስገኘት ጥያቄ ማቅረባቸውን እየቀጠሉ የሚጓዙ ተማሪዎች ለመለየት ጠንካራ እምነት አለው። የተማሪውን የቀለም ትምህርት ፍላጎቶች እና ችሎታዎች ላይ ግልጽ የሆነ እይታ እንዲኖረን |

| | | |
|---|---|---|
| | | ጥረት በምናደርግበት ጊዜ፣ ለመግባት ዕድል አላቸው ተብሎ የሚገመቱ ተማሪዎች ብቻ በማመልከቻ ሂደቱ የቃለ-መጠይቁ ክፍል እንዲካፈሉ እንጠይቃለን።<br><br>ቃለ-መጠይቅ፣ ለሁሉም አመልካቾች ጥቅም ላይ በሚውለው ውስጣዊ የደረጃ መጠን (rubric)፣ ወደፊት ለሚመጣው ተማሪ፣ የብቁነት የውጤት ደረጃ (score) ሲቆጠር፣ 25% በሆነው የቃለ-መጠይቅ ውጤት ደረጃዎቹ ላይ የሚገመገም ይሆናል።<br><br>በጤና ሁኔታዎች እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY21-22 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ ሊከናወን ይችላል። |
| የፍላጎት የዳሰሳ ጥናት | 10% (ለማጠናቀቅ ብቻ) | የፍላጎት የዳሰሳ ጥናት፣ በMSDC ማመልከቻ ውስጥ የሚገኝ እና በተጠናቀቀበት ጊዜ ብቻ ደረጃ ውጤት ይሰጠዋል። ሁሉም አመልካቾች ይህን ክፍል፣ እንደ የ'My School DC' ሎተሪ ማመልከቻ አንዱ አካል አድርገው ማጠናቀቅ አለባቸው። የዳሰሳ ጥናቱ፣ የወደፊት ተማሪ ከሆኑት፣ የትምህርት ቤት ተሞክሮአቸው ምን ለማግኘት ተስፋ እንደሚያደርጉ፣ እና ለትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ምን ሊያመጡ እንደሚችሉ ለማወቅ በጥልቀት ሊያሳይ የሚችል ሆኖ ያገለግላል። በተጨማሪም፣ የፍላጎት የዳሰሳ ጥናት፣ የወደፊት ተማሪ ሊሆን የሚችሉትን የጊዜ ሰሌዳ ለመቆጣጠር እና የቀለም ትምህርት የአካዳሚ ተሳትፎ/ምደባን ለመወሰን ይረዳል። |
| ድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | 35% | 'CHEC'፣ የወደፊት ተማሪውን የትምህርት ቤት ውስጥ ተሞክሮ የበለጠ ለመረዳት እና ለሪፖርት ካርዳቸው ይዘትን ለመስጠት፤ የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠቀምበታል።<br><br>CHEC፣ በአጠቃላይ ሁለት የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠይቃል። በተጠየቀው አስተማሪ አንድ ብቻ ተሞልቶ ከተጠናቀቀ፣ በገባው አንድ ድጋፍ መስጫ (recommendation) ላይ መሠረት በማድረግ ተማሪውን እንገመግማለን። ምንም ዓይነት ድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ካልገቡ፣ ትምህርት ቤቱ በሪፖርት ካርድ ምልከታ እና በቃለ-መጠይቁ ውስጥ ያሉትን ነጥቦች ያከፋፍላቸዋል።<br><br>በየግል የገቡ የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations)፣ የድጋፍ ሰጪው፣ የተማሪውን በእጅጉ የተሟላ ምስል በተቻለ መጠን እንዳላቸው ለማረጋገጥ፤ በራሳቸው በኩል - ተማሪዎች እና ቤተሰቦችን ክትትል እንዲያደርጉ አጥብቀን እናበረታታለን። |

# SY21-22 የ'Duke Ellington' የስነጥበባት (ARTS) ትምህርት ቤት: የመግቢያ (Admission) ሂደት የደረጃ መጠን (Rubric)

ከ9-12 ለሆኑ የክፍል ደረጃዎች**

**ስለ 'Ellington' የመግቢያ (Admissions) መስፈርት:** በ'Duke Ellington' የስነጥበባት (ARTS) ትምህርት ቤት (DESA)፣ ለስዕል የጋለ ስሜት ያላቸውን፣ ለማህበረሰቡ ቁርጠኝነትን የሚያሳዩ እና የስነጥበብ ዜጎችን የሚያበረታቱ፣ እና ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ አልፈው መስራት የሚችሉ – ጥብቅ የሆነ የኮሌጅ ቅድመ-ዝግጅት የጊዜ ሰሌዳን ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ፤ ቅድመ-ባለሙያዊ የሆነ የስዕል ስልጠናዎችን ለመውሰድ ትጋትን በማሳየት የሚሰሩ ምሁሮችን እንፈልጋለን። ምንም እንኳን የውጤት ደረጃቸው ወይም ያስመዘገቡት ውጤቶች ምርጥ ነው ባይባልም እንኳን፤ በሁሉ የክፍል ስራዎቻቸው ላይ ጥረት የሚያደርጉ፣ በይበልጥ ስኬታማ የሆኑ አመልካቾችን እንፈልጋለን።

**ስለ 'Ellington' የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በ'Duke Ellington' የስነጥበባት (ARTS) ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ሁሉም አመልካቾቻችን፣ እንደ መጀመሪያ የማመልከቻቸው አካል አድርገው፤ ጽሁፍ (essay)፣ ሪፖርት ካርድ፣ እና ሦስት የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) እንዲያስገቡ እንጠይቃለን። ከዚያም በኋላ፣ ሁሉንም አመልካቾቻችንን ወደ መደመጥ (audition) ወይም ፖርትፎሊዮ (portfolio) ምልከታ እንዲሳተፉ እንጋብዛቸዋለን። ለመግቢያ፤ በአነስተኛነት ሊገኝ የሚገባ (minimum) የGPA የውጤት ደረጃ (Score) የለም።

| **የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች** | **መለኪያ (Weight)** | **ማስታወሻዎች:** |
|---|---|---|
| የሪፖርት ካርድ ምልከታ (GPA እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት/Attendance) | 10% | የ'Duke Ellington' የስነጥበባት (ARTS) ትምህርት ቤት፤ የውጤት ደረጃ (GPA) እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (Attendance) የመረጃ ስብስብ (data)ን፣ እንደ ሪፖርት ካርድ ምልከታ አንዱ አካል በማድረግ ይመለከተዋል። በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) GPA ወይም አስፈላጊ የሆነ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (Attendance) የለም፤ ነገር ግን ማመልከቻው፣ ለመግባት (admission) እንዲታይ ለማድረግ፣ የሪፖርት ካርድ መግባት አለበት።<br><br>የ'D' ወይም የ'F' ውጤት ያገኙ ተማሪዎች፣ ወይም ከ5 በላይ መቅረቶችን በሪፖርት ካርድ/በሂደት ሪፖርቱ ላይ ያስመዘገቡ፤ የበለጠ መረጃዎችን ወይም ዝርዝሮችን በቤተሰባቸው ቃለ-መጠይቅ ጊዜ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። |
| ጽሁፍ (Essay): በMSDC ማመልከቻ ውስጥ | 10% | እንደ ቃለ-መጠይቁ፣ በፕሮግራማችን ላይ የተማሪውን ፍላጎት ለማወቅ፣ ለማህበረሰቡ ያላውን ቁርጠኝነት፣ እና የግል ጽናት ተሞክሮን ለማንጸባረቅ፤ ጽሁፉ (essay)ን በጥቅም ላይ ያውላል። ይህ ጽሁፍ (essay)፣ በMSDC ማመልከቻ አማካኝነት የሚጠናቀቅ ነው።<br><br>**ማስታወሻ:** ተማሪው እንደሚያመለክትበት መምሪያ መሠረት፤ ተጨማሪ ጽሁፎችን (essays)፣ የጽሁፍ ናሙናዎች፣ ወይም ቁሳቁሶች (materials)ን በMy School DC' ማመልከቻMy School DC' ማመልከቻ አማካኝነት ወይም በ'Acceptd™ Virtual Audition Platform' - በSY21-22 የመግሪያ ጊዜ ውስጥ በስራ ላይ የሚውል አዲስ ፖርታል አማካኝነት፤ እንዲያስገቡ የሚያስፈልጋቸው ሊሆን ይችላል። እነዚህ ተጨማሪ ቁሳቁሶች (materials)፣ እንደ የመደመጥ (Audition)/የፖርትፎሊዮ (Portfolio) ምልከታ ክፍል አንዱ አካል ሆኖ የሚገመገም ይሆናል።<br><br>ጽሁፎች (Essays)፤ በእያንዳንዱ የስነጥበብ መምሪያ እና የመግቢያ (Admissions) ቡድን ምልከታ የሚደረግበት ይሆናል። ምንም እንኳን ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ወቅት በሙሉ አዘውትረው መፃፍ ቢጠበቅባቸውም፣ በቴክኒካል የአፃፃፍ ችሎታዎች ላይ፤ እንደ ሰዋሰውና ቃላት (grammar and vocabulary) ላይ የጽሁፎች (essays) ግምገማ ላይ ለብቻው ያተኮረ አይሆንም። |
| ድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | 10% | የ'Duke Ellington' የስነጥበባት (ARTS) ትምህርት ቤት፣ የተማሪውን የትምህርት ቤት ውስጥ ተሞክሮ የበለጠ ለመረዳት እና በቀለም ትምህርት የሚያገኙት ውጤቶች ይዘትን ለመስጠት፤ የአስተማሪን ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠቀማል።<br><br>የ'Duke Ellington' የስነጥበባት (ARTS) ትምህርት ቤት፣ ሦስት የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠይቃል። ሆኖም፣ ተማሪዎች ላልተሟሉ ወይም ለጠፉ የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ቅጣት አይደርስባቸውም፤ እና በተገኘው የድጋፍ መስጫዎች |

| | | |
|---|---|---|
| | | (recommendations) ላይ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ እንዲገመገም ይደረጋል። <br><br> በየግል የገቡ የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) በራሳቸው በኩል እንዲከታተሉ እና የድጋፍ ሰጪውን የኢሜል አድራሻዎች ትክክለኛነት እንዲያረጋግጡ፤ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ክትትል እንዲያደርጉ አጥብቀን እናበረታታለ። መደመጦቹ (auditions)፣ የማመልከቻ የማብቂያ ቀንን ወዲያውኑ ተከትሎ የሚከናወን ሆኖ በመገኘቱ፣ ድጋፍ ሰጪዎች (recommenders)፣ የሚፈለገውን የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) በቂ በሆነ ጊዜ ማዘጋጀት እንዲችሉ፣ አመልካቾች ከማብቂያው ቀነ-ገደብ በሚገባ ቀደም ብሎ ማመልከቻቸውን እንዲያስገቡ እናበረታታለን። |
| የመደመጥ (Audition)/የፖርትፎሊዮ (Portfolio) ምልከታ | 50% | ሁሉንም አመልካቾች ወደ መደመጥ (audition) ወይም ፖርትፎሊዮ (portfolio) ምልከታ እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል። በተመረጡት መምሪያቸው መሠረት፣ ተማሪዎች ተጨማሪ ቁሳቁሶችን (materials)፤ ጉድ ፎተግራፍን ጨምሮ (ከዚህ በፊት በMy School DC' ማመልከቻ በኩል ካልገባ)፣ ፖርትፎሊዮ (portfolio)/የስራ ናሙና፣ ወዘተ… እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ። አንዳንዶቹ እነዚህ ቁሳቁሶች (materials)፣ (እንደ የተፃፈ ናሙናዎች ያሉ) በMy School DC' ማመልከቻ ወይም በ'Acceptd™ Virtual Admissions Platform' አማካኝነት የሚገቡ ሲሆን፣ ነገር ግን በመደመጥ (Audition)/ፖርትፎሊዮ (Portfolio) ምልከታ አንዱ አካል በመሆን ይገመገማል። ለተጨማሪ መረጃ፣ Audition Proceduresን ይመልከቱ። <br><br> በጤና መመሪያ እና የቤተሰቡን ሁኔታ ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ፣ የመደመጥ ዝግጅቶች (auditions)፣ ተቀባይነት ባለው የመደመጫ (Audition) መድረክ አማካኝነት፣ በርቀት በምናባዊ (virtually) ይካሄዳል። ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ ቤተሰቦች ወደ DESA ድህረ-ገጽ መሄድ አለባቸው። <br><br> ዝርዝር የሆነ ትዕዛዛቶችን፣ የመደመጥ (Audition)/የፖርትፎሊዮ (Portfolio) ምልከታን ለማጠናቀቅ እርዳታ ወይም እንክብካቤዎች ለሚያስፈልጓቸው ማንኛውም ተማሪዎች፣ መረጃን እና ቀጣይ እርምጃዎችን ጨምሮ፤ ለሁሉም ተማሪዎች ይላካል። በተጨማሪም፣ በዓመቱ ሙሉ በ'የDESA ድህረ-ገጽ ላይም ማግኘት ይቻላል። |
| **መደመጡን (audition) እና የማመልከቻውን ምልከታ አቀራረብን ያለፉ ተማሪዎች ብቻ፣ በሂደቱ ቀጣይ እርምጃዎችን በመቀጠል እንዲያከናውኑ ይጋበዛሉ።** | | |
| የመምሪያው የማቅረቢያ ምሽት (Department Presentation Night) | መሳተፍ ያስፈልጋል* | የመምሪያው የማቅረቢያ ምሽት (Department Presentation Night) አላማው፤ መደመጣቸውን (audition) ያለፉ ቤተሰቦችን እና ተማሪዎች፣ ከመምሪያው ጋር ተገናኝተው ለመምሪያው-ልዩ ሆኖ፣ የሚጠበቁባቸውን ለመመልከት እና በዚያ ዙሪያ ስላለው ጥናት ጥያቄዎች ለመጠየቅ ነው። |
| የቀለም ትምህርት ምደባ ግምገማ (Academic Placement Assessment) | መሳተፍ ያስፈልጋል* | በ'Duke Ellington' የስነጥበባት (ARTS) ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ሁሉንም አዲስ መጪ ተማሪዎች፤ መግባት ከቻሉ እና ከተመዘገቡ፣ ለተማሪው ተገቢ የሆነ ምደባን እንድናደርግ እንዲረዳን፣ እና ማንኛውንም የሚያስፈልጉ እርዳታዎችን ለመለየት፤ የቀለም ትምህርት ምደባ ግምገማ (Academic Placement Assessment) እንዲያጠናቅቁ እንጠይቃለን። የቀለም ትምህርት ግምገማው ለመግቢያው (admission) ወደ ተማሪው ብቁነት ውጤት ማስገኛነት በማይገባበት ጊዜ፣ ሁሉም አመልካቾች ይህን እርምጃ እንዲያጠናቅቁ እንጠይቃለን። ከግምገማው የተገኙ ውጤቶች፣ በቃለ-መጠይቁ ጊዜ ውይይት ይደረግበታል። በጤና ሁኔታዎች እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY21-22 ውስጥ፣ የቀለም ትምህርት ምደባ ግምገማው፣ በርቀት (virtually)፣ ሊከናወን ይችላል። |
| ቃለ-መጠይቅ | 10% | 'Duke Ellington' የስነጥበባት (ARTS) ትምህርት ቤት፣ ለፕሮግራማችን የጋለ ስሜት ያላቸውን፣ ለማህበረሰቡ ቁርጠኝነትን የሚያሳዩ፣ እና ጽናትን ማሳየት የሚችሉ ተማሪዎችን ለይቶ ማውጣትን አበክሮ ያምንበታል። <br><br> ተማሪዎች ወደ ቃለ-መጠይቁ፤ ከቤተሰብ አባል ጋር (ከወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ፣ ወይም ከሌላ የቅርብ የቤተሰብ አባል) ወይም ሌላ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው ጋር (ለምሳሌ እንደ አሰልጣኝ፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት መሪ/mentor)፤ ተማሪውን በመደበኛነት ከሚረዷቸው ጋር አብረው እንዲካፈሉ እንጠይቃቸዋለን። |

| | | |
|---|---|---|
| | | በጤና ሁኔታዎች እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY21-22 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ ሊከናወን ይችላል። |
| የመግቢያ (Admissions) የኮሚቴ ምልከታ | 10% | የቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የመግቢያ (Admissions) ኮሚቴው (ርዕሰ መምህር፣ የምዝገባ ዳይሬክተር፣ የተማሪ ጉዳዮች ዳይሬክተር፣ አስተማሪዎች እና/ወይም የመምሪያው መሪዎች) አጠቃላይ ማመልከቻውን የሚመለከቱ እና የመጨረሻ የብቁነት ውሳኔዎችን ለመስጠት የመጨረሻ አስተያየትን ይሰጣሉ። ተማሪዎች በየግላቸው የሚገመገሙ እና በትምህርት ቤቱ የስነጥበብ (arts) ፕሮግራሞች ከሚፈልጋቸው ነገሮች ጎን ለጎን የሚመዘን ይሆናል። ከእያንዳንዱ የስነጥበብ (art) መምሪያ ውስጥ ከፍተኛ ውጤቶችን ያገኙ ተማሪዎች፣ ብቁ ሆነው ይለያዩ። |

*በዚህ ዝግጅት ላይ መሳተፍ ያስፈልጋል። ሆኖም፣ በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም በጊዜ ሰሌዳ መጋጨት ምክንያት መካፈል ካልቻላችሁ፣ አማራጭ ማስተካከያዎች ሊደረጉ ይችላሉ። እባክዎን ትምህርት ቤቱን በቀጥታ ያነጋግሩ።

**DESA፣ ወደ 11ኛ እና 12ኛ ክፍል የሚገቡ አመልካቾች ላይ እና፤ ከስነጥበብ (arts) ትምህርት ቤት እስከተላለፉ ድረስ እና በቂ የሆነ የስነጥበባት ክሬዲቶች (arts credits) እስካላቸው ድረስ እና ሊያጠኑት ባሰቡት ኮርሶቻቸው ጋር በተመሣሣይነት እስካላቸው ድረስ ምልከታ ያደርጋል።

# በSY21 -22 የኩሌጅ (Coolidge) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ: የመግቢያ (Admission) ሂደት የደረጃ መጠን (Rubric)

*ለክፍል ደረጃዎች፡ 9 እና 10*

**ስለ ቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ የመግቢያ (Admissions) መስፈርት**:
የቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ በኩሌጅ (Coolidge) ውስጥ፣ **COLTS** መሆን የሚፈልጉ ምሁራኖችን ይፈልጋል:

> የቀለም ትምህርት ግቦቻቸውን ለማሳካት እና ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ ጥብቅነትን እና ጽናትን ራስን ማስተካከል የሚጠይቅ **ቁርጠኝነት (Committed)**።
> ስለነርሱ እና ስለእኩዮቻቸው የማደግ ችሎታ **ብሩህ አመለካከት ያላቸው (Optimistic)።**
> ታማኝነትን፣ ተጠያቂነትን፣ እና የትምህርት ቤታችንን ማህበረሰብን እሴቶችን ***መሪዎች* በመሆን (Leader)**የሚሸከሙ።
> በሚያደርጉት እርምጃዎች ላይ አስተዋይ በመሆን እና በዓለም ላይ አዎንታዊ አስተዋጽዖ ለማምጣት በመስራት **ህብረተሰብን መቀየር (Transforming Society)።**

**ስለ ቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ የመግቢያ (Admissions) ሂደት፡**
የመቀበያ ሂደታችን የሚያካትተው ሁሉን አቀፍ የሆነ ምልከታ ለእያንዳንዱ የማመልከቻ ክፍሎች - ሪፖርት ካርዶች፣ ጽሁፍ (essay)፣ እና የአስተማሪ ድጋፍ መስጫዎች (recommendations)። እያንዳንዱ የማመልከቻው ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሰረት ተገምግሟል። ምንም አንድ ክፍል፣ ብቻውን ለብቁነት መወሰኛ ሆኖ አይወሰድም። በቀለም ትምህርት ፕሮግራም ጥብቅነት ምክንያት፣ በGPA ላይ ከፍተኛ አፅንዖት የምንሰጠው እና በቀለም ትምህርት እድገት ላይ ወደላይ ሲያሻቅብ ማየትን የምንመርጠው ይሆናል። በጣም ስኬታማ ሆነው ያገኘናቸው አመልካቾች፣ ለጠንካራ ስራ ቁርጠኝነት ያላቸው ሲሆን ይህንንም በጽሁፋቸው (essay)፣ በድጋፍ መስጫዎች (recommendations) እና በቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ በተጨማሪነት ማስመስከር የቻሉ ናቸው።

የቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ፣ የመጀመሪያ የሆነ ግንኙነቶችን የምንገነባበት እና በማመልከቻ ሌሎች ገጽታዎች ላይ ጎልተው ለመመልከት ያልቻልናቸውን ነገሮች ለማወቅ እድል የሚሰጠን ነው። ለቃለ- መጠይቁ፣ የቤተሰብ አባል፤ ወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ፣ ወይም ሌላ ቅርብ የቤተሰብ አባል ሊሆን ይችላል። ተማሪዎችን በመደበኛነት የሚረዷቸው፣ ሌላ በተማሪው ህይወት ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው፣ እንደ አሰልጣኝ፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት መሪ/mentor፣ ሊሆንም ይችላል። የቃለ-መጠይቁን ጨርሰን ስምወጣ፣ የተማሪውን ማንነት በተሻለ ሁኔታ የምንረዳበት እና ቤተሰቡ እንዴት መማርን እንደሚደግፉ ለማወቅ እንደሚያስችለን ተስፋ አለን።

ሊገኝ ከሚችለው ከ100 ውስጥ 85 ነጥቦችን ያገኙ ተማሪዎች ብቁ ይሆናሉ፤ ሆኖም ይህ ቁጥር ሁሉን አቀፍ በሆነው የአመልካቾች ምልከታ ላይ መሠረት በማድረግ፣ ዓመታዊ የዝቅተኛ ደረጃ የሚስተካከልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

| የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች | መለኪያ (Weight) | ማስታወሻዎች፡ |
|---|---|---|
| የቀለም ትምህርት የመስፈርት ምልከታ (GPA) | 40 ነጥቦች (40/100 ነጥቦች) | ECA ውጤቶችን (GPA) እንደ የቀለም ትምህርት መስፈርት ምልከታ አንዱ አካል አድርጎ ይመለከተዋል። በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) የGPA መስፈርት የለም። ተማሪዎች ለSY2019-20 የመጨረሻ ሪፖርት ካርዳቸውን እና ለSY2020-21 የመጀመሪያ ተርም ሪፖርት ካርድን ማስገባት አለባቸው። የሪፖርት ካርድ/የትምህርት ውጤት ማረጋገጫ እና ውጤቶች፣ ለማመልከቻው የመግቢያ (admission) ሂደት ከግምት ውስጥ እንዲገቡ መግባት አለባቸው።<br><br>ከELA፣ ሳይንስ፣ ሂሳብ እና የኅብረ ትምህርት/ታሪክ ውስጥ ያሉ ክፍሎች፣ GPAን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውሉ እና፤ በቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ የ3.0 ነጥብ GPA ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ነጥብ ያላቸው በተለመደ ሁኔታ ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች ናቸው።<br><br>በSY19-20 የPARCC መሰረዝ ምክንያት፤ DCPS የPARCC ወይም የሌላ ደረጃውን የጠበቀ የፈተና ውጤት እንደ የSY21-22 የመግቢያ (admissions) ፈተናዎች አድርገው አያስገቧቸውም። |
| ድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | 20 ነጥቦች (20/100 ነጥቦች) | ECA፣ 2 የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ይፈልጋል። ECA፣ የአስተማሪ ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations)፣ ለተማሪዎች የአካዳሚክ መዝገብን፣ የጥረታቸውን ደረጃ፣ እና አጠቃላይ በትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸውን ተሞክሮ ይዘትን ለመስጠጥ ይጠቀምበታል። በየግል የገቡ የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) በራሳቸው በኩል እንዲከታተሉ እና የድጋፍ ሰጪው የተማሪውን |

| | | |
|---|---|---|
| | | በእጅጉ የተሟላ ምስል እንዲያስገቡለት ለማድረግ፤ ተማሪዎች እና ቤተሰቦችን ክትትል እንዲያደርጉ አጥብቀን እናበረታታለ። ሆኖም፣ ተማሪዎች ላልተሟሉ ወይም ለጠፉ የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ቅጣት አይደርስባቸውም፤ ስለሆነም፤ በተገኘው የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ላይ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ እንዲገመገም ይደረጋል። |
| ጽሁፍ (Essay): በMSDC ማመልከቻ ውስጥ | 25 ነጥቦች (25/100 ነጥቦች) | ጽሁፉ (essay)፣ የተማሪን ፍላጎት እና የችሎታ ደረጃን ለማግኘት ይጠቅማል። የመግቢያ (admissions) ቡድኑ የተማሪውን በECA ውስጥ ያለውን ፍላጎት፣ ለመማር ያለውን ቁርጠኝነት፣ እና የወደፊት ግቦችን ለመለካት ጽሁፉን (essay) ይመለከታል። ጽሁፉ (essay)፣ በተጨማሪም እንደ የተማሪው ሰዋሰው (grammar)፣ ቃላት (vocabulary) እና ቴክኒካል የአፃፃፍ ደረጃ፣ የመጀመሪያ ናሙና ሆኖ ያገለግላል። |
| የቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ | 15 ነጥቦች (15/100 ነጥቦች) | ECA፣ ተማሪዎች ወደ ቃለ-መጠይቁ፤ ከቤተሰብ አባል ጋር (ከወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ፣ የቅርብ የቤተሰብ አባል) ወይም ሌላ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው ጋር (እንደ አሰልጣኝ፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት መሪ/mentor)፤ ተማሪዎችን በመደበኛነት ከሚረዷቸው ጋር አብረው እንዲካፈሉ ይፈልጋል።<br><br>በጤና ሁኔታዎች እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY21-22 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ ይከናወናል። |

# SY21-22 'McKinley Technology' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት: የመግቢያ (Admissions) የደረጃ መጠን (Rubric)

ከ9-11* ለሆኑ የክፍል ደረጃዎች

**ስለ 'McKinley Technology' የመግቢያ (Admissions) መስፈርት:** የ'McKinley Technology' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በSTEM ትኩረት ያደረገ ትምህርት ቤት ሆኖ፣ ከሦስት 'National Academy Foundation (NAF) አካዳሚዎች ውስጥ፣ ተማሪዎች እንዲመርጡ: የ'Information Technology'፣ ምህንድስና (Engineering) እና Biotechnology። ለመማር፣ በማህበረሰባቸው ውስጥ ክብርን ያገኙ፣ ፈታኝ ነገሮችን ተቀብሎና በነዚህ ፈታኝ ነገሮች ውስጥ በመስራት መፍትሄዎችን የሚፈልጉ፤ የጋለ ስሜት ያላቸውን ምሁራኖችን እንፈልጋለን። በጣም ስኬታማ የሆኑ አመልካቾች፣ ፈጣን የሆነ እርምጃን በመማር ሂደቱ ላይ የሚወስዱ፣ አዲስ ነገርን ለመሞከር ፍላጎት ያላቸው፣ ስለወደፊት እቅዳቸው ትኩረት የሚሰጡ፣ እና በSTEM-እና ተያያዥ የሆኑ መስኮች ላይ ፍላጎት ያላቸው ሆነው አግኝተናቸዋል። ከቀለም ትምህርት ቁርጠኝነታቸው ጋር፣ በብዙ ነገሮች ብስለትን ያላቸው ( well-rounded) ግለሰቦችን እንፈልጋለን።

**ስለ 'McKinley Technology' የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** የ'McKinley Technology' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በመጀመሪያ ሁሉንም የአመልካቾች ሪፖርት ካርዶችን እና የድጋፍ መስጫ ደብዳቤዎችን (recommendation letters) ይመለከታል። በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) መስፈርት ባይኖርም፣ ስኬታማ የሆኑ አመልካቾች በተለምዶ በአማካኝ 3.0 GPA የሚጠጉ ወይም የሚበልጡ፣ እና በመካከለኛ (middle) ትምህርት ቤት ውስጥ በሂሳብ፣ በሳይንስ፣ እና በእንግሊዘኛ ኮርሶች፤ ስኬታቸውን ያንጸባረቁ። ሆኖም፣ አነስተኛ GPAዎች እና የፈተኛ ውጤቶች ያሏቸው ተማሪዎች፣ ትክክለኛ የሆነ እርዳታን እና ስልቶችን ሲያገኙ ስኬትን ማግኘት እንደሚችሉ ለማወቅም ችለናል። በSY19-20 የPARCC መሰረዝ ምክንያት፤ DCPS የPARCC ወይም የሌላ ደረጃውን የጠበቀ የፈተና ውጤት እንደ የSY21-22 የመግቢያ (admissions) ፈተናዎች አድርገው አያስገቧቸውም።

የሪፖርት ካርድ እና የድጋፍ መስጫ ደብዳቤዎች (recommendation letters)፤ በመግቢያ (admission) ሂደቱ ውስጥ የመጀመሪያ ቦታ የሚሰጣቸው፣ ሙሉ የሆነ ማለፍ የሚገባው መስፈርት (Threshold criteria) ናቸው። በነዚህ መስፈርት መሠረት፣ ከፍተኛ የውጤት ደረጃን ያስመዘገቡ አመልካቾች፣ ቀጣይ በሆነው የ(admission) ሂደት ውስጥ፣ የቡድን ቃለ-መጠይቅ እና የመፃፍ ክፍለጊዜ (Writing Session) እንዲካፈሉ ይጋበዛሉ። ከዚህ በመቀጠል፣ ከማመልከቻው ምልከታ ላይ ከፍተኛ የሆነ የተጠራቀመ የውጤት ደረጃ ያላቸው ተማሪዎች፣ የቡድን ቃለ-መጠይቅ እና የመፃፍ ክፍለጊዜ (Writing Session)፤ ለመግቢያ (admission) ብቁ እንዲያደርጋቸው ተደርጎ የሚቀመጥ ሲሆን የሚችል እና የግል ቃለ-መጠይቅን ማጠናቀቅ ላያስፈልግ ይችላል። በተጠራቀመ የውጤት ደረጃዎቻቸው መሠረት፣ ሌሎች ተማሪዎች በሙሉ፣ በሁለተኛ፣ የግል ቃለ-መጠይቅ ውስጥ፣ የብቁነት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት እንዲካፈሉ ሊጠየቁ ይችላሉ። ወደ ቃለ-መጠይቁ የተጋበዙ ተማሪዎች፣ በቀጣይነት ለሚደረገው ምልከታ በቃለ-መጠይቅ ውስጥ እንዲካፈሉ ይጠየቃሉ።

አጠቅላይ 400 ሊሆኑ የሚችሉ ነጥቦች ለመግቢያ (admissions) ሂደቱ አለ። አመልካቾች ከዚያ በኋላ፣ ለመግባት ብቁነታቸውን ለመወሰን፣ በጠቅላላ ነጥባቸው ደረጃ ይሰጣቸዋል። በተጠራቀመ ማመልከቻዎች ነጥቦቻቸው ላይ መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ደረጃ ይሰጣቸዋል፣ ከዚህ በፊት በማመልከቻ ምልከታቸው ላይ መሠረት በማድረግ ብቁነት ከተሰጣቸው ተማሪዎች ጋር፣ የቡድን ቃለ-መጠይቅ፣ እና የጽሁፍ ክፍለጊዜ (Writing Session) በመጀመሪያ ጊዜ ብቻ፣ ወይም የመጨረሻ ክፍል ወደሆነው፣ ለብቻቸው ቃለ-መጠይቅን እንዲወስዱ በተጋበዙ ተማሪዎች በመከተል፣ አጠቅላይ የተጠራቀመ ነጥብ ቅደም ተከተል ደረጃ ይሰጣል።

| **የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች** | **መለኪያ (Weight)** | **ማስታወሻዎች:** |
|---|---|---|
| የማመልከቻ ምልከታ (ሪፖርት ካርድ እና ድጋፍ መስጫዎች/recommendations) | 25%<br><br>(ይህ ክፍል፣ አጠቃላይ የሆነ 100 ነጥቦች አሉት) | የMcKinley Technology HS የደረጃ ውጤቶች (GPA) እየተመለከተ ባለበት ጊዜ፣ ምንም በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) የGPA መስፈርት የለም።<br><br>በማመልከቻው ምልከታ ወቅት፣ የደረጃ አሰጣቶች በ60% የሚመዘን እና በድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ደግሞ በ40% የሚመዘን ነው። በSY19-20 የPARCC መሰረዝ ምክንያት፤ DCPS የPARCC ወይም የሌላ ደረጃውን የጠበቀ የፈተና ውጤት እንደ የSY21-22 የመግቢያ (admissions) ፈተናዎች አድርገው አያስገቧቸውም።<br><br>የእያንዳንዱ አመልካች አጠቃላይ GPA ከግምት ውስጥ ይገባል፣ ሆኖም ከዋናው ክፍሎች ውስጥ ያሉት ደረጃዎች ለመግባት እንዲችሉ፣ በጣም በከባድ ሁኔታ የሚታዩ ይሆናል። |
| **ከዚህ በላይ በሚታየው መስፈርት መሠረት የተማሪዎች ማመልከቻዎች ደረጃ ይሰጣቸዋል። ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን ተማሪዎች (top students)፣ ወደ ቡድን ቃለ-መጠይቅ እና የጽሁፍ ክፍለጊዜ (Writing Session) ክፍል ወደሆነው የመግቢያ (admissions) ሂደት ይጋበዛሉ።** | | |
| የቡድን ቃለ-መጠይቅ | 25% (100 | 'McKinley Technology' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ለፕሮግራማችን የጋለ ስሜት |

| | | |
|---|---|---|
| | ነጥቦች) | ያላቸውን እና ለማህበረሰቡ ትጋትን የሚያሳዩ እንዲሁም ጽናትን የሚያሳዩ ተማሪዎችን ለይቶ ማውጣትን አበክሮ ያምንበታል። የመጀመሪያው ቃለ-መጠይቅ፣ የቡድን ቃለ-መጠይቅ ሆኖ ከሌሎች አመልካቾች ጋር ይደረጋል።<br><br>በጤና ሁኔታዎች እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY21-22 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ ሊከናወን ይችላል። |
| የመፃፍ ክፍለጊዜ (Writing Session) | 25% (100 ነጥቦች) | ልክ እንደ ቃለ-መጠይቁ፣ McKinley፣ የመፃፍ ክፍለጊዜ (Writing Session) ተጠቅሞ፣ በፕሮግራማችን ውስጥ ያለውን የተማሪውን ፍላጎት፣ ለማህበረሰቡ ቁርጠኝነት የሚያሳዩ፣ እና የግል ጽናታቸውን የማንጸባረቅ ልምዶች ያላቸውን ተማሪዎች ለማግኘት ይጠቀምበታል። የመፃፍ ክፍለጊዜ (Writing Session)፣ በSY21-22 ውስጥ በርቀት በምናባዊ (virtually) ሊካሄድ ይችል ይሆናል።<br><br>በዚህ የመፃፍ ክፍለጊዜ (Writing Session) የናሙና ስብሰባ ጊዜ፣ በተለየ መልኩ በቃላት፣ በሰዋሰው፣ ወዘተ… ላይ ግምገማ ሳይደረግ፣ ተማሪዎች ጥያቄዎችን በሚገባ እንዲመልሱ እና የተማሪውን አጠቃላይ በተፃፈ ጽሁፍ አማካኝነት መግባባት የሚችልበትን ችሎታዎች ለመለካት እንመለከታለን። |
| **ከዚህ በላይ በሚታየው መስፈርት መሠረት የተማሪዎች ማመልከቻዎች ደረጃ ይሰጣቸዋል። ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን ተማሪዎች (top students) በብቸኝነት ብቁነትን እንዲያገኙ በተጠራቀመ ማመልከቻዎች፣ የቡድን ቃለ-መጠይቅ፣ እና የጽሁፍ ክፍለጊዜ (Writing Session) ውጤት እስካሁን ሳይኖር፣ ወይም የመጨረሻ ክፍል ወደሆነው፣ ለብቻቸው ቃለ-መጠይቅን እንዲወስዱ ይጋበዛሉ።** | | |
| ለየብቻ የሚደረግ (Individual) ቃለ-መጠይቅ | 25% (100 ነጥቦች) | ልክ እንደ ቡድን ቃለ-መጠይቅ፤ የብቻ ቃለ-መጠይቅም፤ የተማሪውን በትምህርት ቤታችን ውስጥ ያለውን ፍላጎት የመለኪያ ዕድል የሚሰጥ፣ የራሳቸውን የሆነውን ተሞክሮዎች የሚወያዩበት፣ እና ከ'McKinley' ሰራተምፐች ጋር ተማሪዎች የየግል ግንኙነት እንዲያደርጉ የሚፍቅድላቸው እና/ወይም ተማሪዎች የበለጠ ተገቢ የሆነ ምላሾችን ለጥያቄዎች እንዲሰጡ፣ እንዲሁም ከ'McKinley' ፕሮግራም እና ባህል ጋር ለመለማመድ እና ጥያቄዎችን የሚጠይቁበት ይሆናል።<br><br>በጤና ሁኔታዎች እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY21-22 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ ሊከናወን ይችላል። |

*የ'McKinley Technology' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወደ 11ኛ ክፍል የሚገቡ - አመልካቹ በቂ የሆነ ክሬዲቶች እስካለው ድረስ፣ በተመሳሳይ የፕሮግራም ጥናት ውስጥ ለመግባት፣ ወደ ትምህርት ቤቱ የምርቃት መስፈርቶችን በማሟላት በትክክለኛ ጎዳላ ያሉትን አመልካቾች ይመለከታል።

## SY21- 22 የ'PHELPS የምህንድስና (ARCHITECTURE)፣ የግንባታ እና የኢንጂነሪንግ (CONSTRUCTION, AND ENGINEERING) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የደረጃ መጠን (Rubric)

ከ9-12 ለሆኑ የክፍል ደረጃዎች

**ስለ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመግቢያ (Admissions) መስፈርት:** በ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ችግሮችን የሚፈቱ፣ በስራ መስክ የቴክኒካል የትምህርት ፕሮግራማችን ላይ ፍላጎት ያላቸው፣ እና መፍትሄን ለማግኘት ሲባል ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ ለመስራት ፈቃደኛ የሆኑ ምሁራኖችን ማግኘት እንፈልጋለን። ምንም እንኳን የውጤት ደረጃቸው ወይም ያስመዘገቡት ውጤቶች ምርጥ ነው ባይባልም እንኳን፤ በክፍል ስራዎቻቸው ላይ ጥረት የሚያደርጉ፣ በይበልጥ ስኬታማ የሆኑ አመልካቾችን እንፈልጋለን።

**ስለ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ የመግቢያ (admissions) ሂደታችን የሚያካትተው፣ ጽሁፍ (essay)፣ ቃለ-መጠይቅ፣ እና ሁለት የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations)ን በMy School DC ማመልከቻ አማካኝነት ማስገባት ነው። ለእያንዳንዱ እጩ፣ እያንዳንዱን የመግቢያ (Admissions) ክፍሎችን ከግምት ውስጥ የምናስገባ እና ሁሉም አመልካቾች አንድ ዓይነት በሆነ የደረጃ መጠን (rubric) ይመዘናሉ። ምንም አንድ የመግቢያ (Admissions) ክፍል ብቻውን ለብቁነት መወሰኛ ሆኖ አይወሰድም። ሁሉም ተማሪዎች፣ ለመግባት (admissions) ብቁነታቸው እንዲታይላቸው ለማድረግ፣ የቃለ-መጠይቅን ማጠናቀቅ አለባቸው። በSY19-20 የPARCC መሰረዝ ምክንያት፤ DCPS የPARCC ወይም የሌላ ደረጃውን የጠበቀ የፈተና ውጤት እንደ የSY21-22 የመግቢያ (admissions) ፈተናዎች አድርገው አያስገቧቸውም።

እያንዳንዱ ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሰረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚመዘን ይሆናል። በተለምዶ፣ በደረጃ መጠን (rubric) 15 ወይም ከዚያ በላይ ያመጡ ሁሉም ተማሪዎች ብቁ የሚሆኑ ሲሆን፣ ይህ በአነስተኛነት የሚጠበቀውን (minimum) የውጤት ደረጃ፣ በየዓመቱ ለእያንዳንዱ አመልካች፣ ሁሉን አካታች በሆነ ምልከታ አማካኝነት ወደ ዝቅተኛ ደረጃ የሚስተካከልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። በአነስተኛነት ከሚጠበቀው (minimum) የውጤት ደረጃ በላይ ያመጡ ሁሉ አመልካቾች ብቁ ይሆናሉ፤ እንዲሁም አመልካቾች በተጠራቀመው የደረጃ መጠን (rubric) መሠረት አድርጎ በተከተለ አሰራር ደረጃ እንዲያገኙ ይደረጋል።

| የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች | መለኪያ (Weight) | ማስታወሻዎች: |
|---|---|---|
| የቀለም ትምህርት የመስፈርት ምልከታ (GPAን እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት/attendance የሚያካተተ) | 40% ( 12/ 30 ነጥቦች) | የ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የውጤት (GPA)ን እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance)ን፣ እንደ የቀለም ትምህርት የመስፈርት ምልከታ ይመለከተዋል። ምንም ዓይነት፣ በአነስተኛነት የሚጠበቅ (minimum) GPA እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) መለኪያ አያስፈልግም፤ ነገር ግን ሪፖርት ካርድ መግባት አለበት። በSY19-20 የPARCC መሰረዝ ምክንያት፤ DCPS የPARCC ወይም የሌላ ደረጃውን የጠበቀ የፈተና ውጤት እንደ የSY21-22 የመግቢያ (admissions) ፈተናዎች አድርገው አያስገቧቸውም።<br><br>በተለምዶ፣ በፕሮግራማችን ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች የ2.5 GPA ወይም ከዚያ በላይ እና የ90% ወይም ከዚያ በላይ በክፍል ውስጥ መገኘት (in-seat attendance) ያላቸው ሲሆን፤ ሆኖም፣ አነስተኛ GPAዎች ያሏቸው ተማሪዎች፣ ትክክለኛ የሆነ እርዳታን እና ስልቶችን ሲያገኙ ስኬትን ማግኘት እንደሚችሉ ማወቅም ችለናል። |
| ቃለ-መጠይቅ | 40% (12/ 30 ነጥቦች) | የ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በፕሮግራማችን ላይ ፍላጎት ያላቸውን፣ እና ችግሮችን ለመፍታት ፈቃደኝነትን የሚያሳዩ ተማሪዎች ለመለየት ጠንካራ እምነት አለው። የወደፊት ተማሪዎቻችንን ለመተዋወቅ የምንፈልግ እና ይህንንም ለማድረግ የቃለ-መጠይቁ ጠቃሚ መንገድ ነው።<br><br>ተማሪዎች ወደ ቃለ-መጠይቁ፤ ከቤተሰብ አባል ጋር (ከወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ፣ ወይም ከሌላ የቅርብ የቤተሰብ አባል) ወይም ሌላ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው ጋር (እንደ አሰልጣኝ፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት መሪ/mentor)፤ ተማሪዎችን በመደበኛነት ከሚረዷቸው ጋር አብረው እንዲካፈሉ እንጠይቃቸዋለን።<br><br>በጤና ሁኔታዎች እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY21-22 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ ሊከናወን ይችላል። |

| | | |
|---|---|---|
| | | ቃለ-መጠይቅ፣ ለሁሉም አመልካቾች ጥቅም ላይ በሚውለው ውስጣዊ የደረጃ መጠን (rubric)፣ ለተማሪውን የብቁነት የውጤት ደረጃ (score) ሲቆጠር፣ 40% በሆነው የቃለ-መጠይቅ ውጤት ደረጃዎቹ ላይ የሚገመገም ይሆናል። |
| ጽሁፍ (Essay): በMSDC ማመልከቻ ውስጥ | 10% ( 3/ 30 ነጥቦች) | ልክ እንደ ቃለ-መጠይቁ፣ በፕሮግራማችን እና በጽሁፍ ንግግር (communication) ችሎታዎች ላይ የተማሪውን ፍላጎት ምን እንደሆነ ለማወቅ፣ ጽሁፉ (essay)ው ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ ጽሁፍ (essay)፣ እንደ MSDC ማመልከቻ አንዱ አካል በመሆኑ ይጠናቀቃል።<br><br>ጽሁፎች፣ ለሁሉም አመልካቾች ጥቅም ላይ በሚውለው ውስጣዊ የደረጃ መጠን (rubric)፣ ለተማሪውን የብቁነት የውጤት ደረጃ (score) ሲቆጠር፣ 10% በሆነው የጽሁፍ ውጤት ደረጃዎቹ ላይ የሚገመገም ይሆናል። ምንም እንኳን ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ወቅት በሙሉ አዘውትረው መፃፍ ቢጠበቅባቸውም፣ ለጽሁፍ (essay) የደረጃ መጠኑ (rubric)፣ በቴክኒካል የአፃፃፍ ችሎታዎች ላይ፤ እንደ ሰዋሰውና ቃላት (grammar and vocabulary) ላይ ያተኮረ አይሆንም። |
| ድጋፍ የተሰጠባቸው (Recommendations) | 10% ( 3/ 30 ነጥቦች) | የ'Phelps ACE' ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የተማሪውን የትምህርት ቤት ውስጥ ትእሞክሮ የበለጠ ለመረዳት እና ለሪፖርት ካርዳቸው ይዘትን ለመስጠት በማለት፤ የአስተማሪን ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) ይጠቀማል።<br><br>ሁለት ድጋፍ መስጫዎች (recommendations) እንዲቀርቡ እንጠይቃለን። በተጠየቀው አስተማሪ አንድ ብቻ ተሞልቶ ከተጠናቀቀ፣ በገባው አንድ ድጋፍ መስጫ (recommendation) ላይ መሠረት በማድረግ ተማሪውን እንገመግማለን። ምንም ዓይነት ድጋፍ መስጫ (recommendations)ን ካላስገቡ፣ ትምህርት ቤቱ የ10% መጠን (weight) ወደ ቃለ-መጠይቁ ይጨምራል። |

## ‘SCHOOL WITHOUT WALLS’ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት: SY21-22 የብቁነት ‘Rubric’

ለክፍል ደረጃዎች: ከ9 – 12 (ሁሉም የክፍል ደረጃዎች)

**ስለ ‘School Without Walls’ የመግቢያ (Admissions) መስፈርት**: በ ‘School Without Walls’ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስኬትን ያገኘ ተማሪ፤ ኃላፊነት የሚሰማው፣ ልበ-ሙሉ፣ ነገሮችን በቀደምትነት መጀመርን፣ በየቀኑ ወደትምህርት ቤት መምጣት፣ ለቀለም ትምህርት ትኩረት የሚሰጥ፣ እና የትምህርት አሰጣጥ አገልግሎታቸውን እንዲያገኙ የሚጠይቅ ነው። በተጨማሪም፣ በ‘School Without Walls’ ውስጥ ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች፤ ራሳቸውን የቻሉ፣ ጠንካራ የጊዜ አያያዝና አጠቃቀም ችሎታዎች ያላቸው፣ እና የዓለም ዙሪያ ዜጎች የመሆን ፍላጎት ያላቸው ናቸው።

**ስለ ‘School Without Walls’ የመግቢያ (Admissions) ሂደት:** በ‘School Without Walls’ ውስጥ፣ ከዚህ በፊት ከነበረው የትምህርት ዓመት የመጨረሻ ክፍሎቻቸው ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ፤ ሁሉም አመልካቾች ቢያንስ የ3.0 GPA ማግኘት አለባቸው። ለ 9ኛ ክፍል፣ ከፍተኛ የሆኑ በግምት 500 ተማሪዎች ከ3.0 ነጥብ ወይም በላይ GPA ያላቸው፣ በቃለ-መጠይቁ እንዲካፈሉ ይጋበዛሉ። ለቃለ-መጠይቁ የሚጋበዙ ተማሪዎች፣ በሂደቱ ለማለፍ እንዲችሉ፤ በቃለ-መጠይቁ መሳተፍ አለባቸው። ከ10ኛ-12ተኛ ክፍል ለሚደረገው ቃለ-መጠይቅ፤ በመጪው የትምህርት ዓመት ይኖራል ተብሎ በሚጠበቀው ቦታዎች ቁጥር ላይ እና በተቀበልናቸው የማመልከቻ ቁጥር ብዛት ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ ይካሄዳል። ከቃለ-መጠይቁ የውጤት ደረጃ (score) በተጨማሪ፣ በGPA ውጤታቸው ላይ መሠረት ያደረገን የውጤት ደረጃ (score)ን፤ ተማሪዎች ያገኙሉ። የእነዚህ ሁለት የውጤት ደረጃዎች (scores) በአንድነት ተቀናጅተው፣ ለእያንዳንዱ ተማሪ የተጠራቀመ የማመልከቻ የውጤት ደረጃ (score)ን ያስገኙቸዋል። ቃለ-መጠይቁን ያጠናቀቁ ሁሉም ተማሪዎች፣ ብቁ የሚሆኑ እና በተጠራቀመው የማመልከቻ የውጤት ደረጃቸው (score) መሠረት፣ ደረጃ ይሰጣቸዋል።

እያንዳንዱ የመግቢያ (admissions) ሂደት ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሰረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚለካ ይሆናል።

| የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች | መለኪያ (Weight) | ማስታወሻዎች: |
|---|---|---|
| ሪፖርት ካርድ ምልከታ (ቢያንስ 3.0 GPA) | ማለፍ የሚገባው መስፈርት (Threshold criteria) | ‘School Without Walls’፣ የክፍል ደረጃዎችን ብቻ እንደ ሪፖርት ካርድ ምልከታዎች አድርጎ ይመለከታቸዋል። በ‘School Without Walls’ ውስጥ የሚገቡ አመልካቾች፣ ጥብቅ እና ከባድ በሆነው ፕሮግራማችን ውስጥ መጪዎቹ ተማሪዎች፣ ስኬታማ ለመሆን ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣ በቀድሞው የትምህርት ዓመት የመጨረሻው ሪፖርት ካርድ ላይ፣ የ3.0 GPA ወይም ከዚያ በላይ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።<br><br>በ9ኛ ክፍል ውስጥ፣ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው 500 ተማሪዎች ከፍተኛ GPAs ያላቸው፣ ወደ ቃለ-መጠይቁ ይጋበዛሉ። ተመሳሳይ የሆነ GPAዎች በሚኖሩ ጊዜ፤ ከ500 በላይ አመልካቾች ለቃለ-መጠይቅ ይጋበዛሉ።<br><br>‘GPA’ው እንዴት እንደሚሰላ (calculated) ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ [እዚህ](#) ተመልከቱ። |
| በ‘GPA’ው መሠረት፣ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ፣ 3.0 ነጥብ ወይም ከዚያ በላይ ያመጡ፤ ከፍተኛ ደረጃን ያመጡ ተማሪዎች፣ በቃለ-መጠይቁ እንዲካፈሉ ይጋበዛሉ። | | |
| ቃለ-መጠይቅ | ~86% (31/36 ነጥቦች) | ‘School Without Walls’፣ ለፕሮግራማችን የጋለ ስሜት ያላቸውን እና ለማህበረሰቡ ትጋትን የሚያሳዩ እንዲሁም ጽናትን የሚያሳዩ ተማሪዎችን ለይቶ ማውጣትን አበክሮ ያምንበታል።<br><br>በGPA ውጤታቸውን መሠረት በማድረግ፣ ጎበዝ ተማሪዎች (Top students)፣ ከወላጅ/አሳዳጊያቸው ጋር፤ ወደ ፓናል ቃለ-መጠይቅ (panel interview) ይጋበዛሉ። ፓናሉ (panel)፣ ፋክልቲን (faculty)፣ ሠራተኞችን፣ እና በአሁኑ ጊዜ የሚማሩ ተማሪዎችን ያካተተ ነው። ተማሪዎች እና ወላጆች ራሳቸውን በመሆን፣ የሚችሉትን ሁሉ እንዲያደርጉ እንጠይቃለን!<br><br>የሁሉም አመልካች ቃለ-መጠይቆች፣ በአንድ ዓይነት የውስጥ አሰራር የደረጃ መለኪያ (internal rubric)፣ ለ~86% የተማሪው የውጤት ደረጃ (score) በሆነ የቃለ-መጠይቅ ውጤቶችን መበቁጠር ይገመገማል።<br><br>በጤና ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY21-22 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ |

| | | |
|---|---|---|
| | | በማይክሮሶፍት ቲምስ (Microsoft Teams) አማካኝነት ይከናወናል። |
| የGPA የውጤት ደረጃ (Score) | ~14%<br>(5/36 ነጥቦች) | ቃለ-መጠይቁን ያጠናቀቁ ሁሉም ተማሪዎች፣ በGPA ላይ መሠረት ያደረገ፣ ተጨማሪ የውጤት ደረጃ (score)፣ በሚከተለው መመዘኛ መሰረት ያገኛሉ፡<br>• 3.8 እና በላይ – 5 ነጥቦች<br>• 3.5 - 3.79– 4 ነጥቦች<br>• 3.2 - 3.49 – 3 ነጥቦች<br>• 3.0 - 3.19 – 2 ነጥቦች |
| የቃለ-መጠይቅ እና የGPA የውጤት ደረጃዎች (scores)፣ በአንድ ላይ ተደምረው፣ እያንዳንዱን ተማሪ የተጠራቀመ የማመልከቻ የውጤት ደረጃ (score) ያስገኙዋል። ቃለ-መጠይቁን ያጠናቀቁ ሁሉም ተማሪዎች፣ ብቁ የሚሆኑ እና በተጠራቀመው የማመልከቻ የውጤት ደረጃ (score) መሠረት፣ ደረጃ ይሰጣቸዋል። | | |